# ፕሮፌሰር ላሬቦ "ጉድ ስንት ነው? ሁለት፤ ምን ያበዛዋል ውሸት!"

ከሲራክ

ድሮ ገና ድሮ በዘመነ ዘውድ ሃይለስላሴ የደሃውን ልጅ እንዳያስተምሩ በዙሪያቸው የነበሩ ክፉ ባላባቶች ይመክሩቸው እንደነበር ስምቻለሁ፡፡ ግምታቸው የተማረው ወጣት ትውልድ የዘውዱን ስልጣን ያፈራርሳሉ ብለው ስለፈሩ ነበር፡፡ በርግጥም የፈሩት እውነት አልቀረም፡፡ በዚያን ወቅት ያመጠውን ጀግኖቹን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የንጉሱ ደጋፊዎች ሲያከቸለችሉ " **እንቁላልና ስጋ መብላት ሰለቸን**" ብለው ስለጠገቡ ነውም ሲሉ ሰምተናል፡፡ ዛሬ ደግሞ ፕሮፌሰር ሃይሌ ላሬቦ እንዲህ ሲሉ የያኔውን የለውጥ አርበኛ ወጣቶችን ይኮንናሉ፡፡

## ውሸት አንድ፡-

"የሚገርመው ከእነዚህ ግለሰቦች፣ የጥቂቶቹ ወላጆች በአገር ክህደት የሚወነጀሉ ቢሆኑም፣ አብዛኞቹ ግን ኢትዮጵያ በታላቅ እንክብካቤ ያስተማረቻቸው፣ አገራቸውን ከነጭ የባርነት ቀንበር አወጥተው፣ በጀግንነት ተዋግተው፣ መልሰው በማቋቋም የገነቧት የአርበኞች ልጆች ናቸው። ጀግኖቹም ራሳቸው የመማር ዕድል ሳያገኙ፣ ትምህርት ቤት አሠርተው፣ አስተማሪ አስቀጥረው፣ ከፍተኛ መሥዋዕት ከፍለው ያስተማሯቸው፣ እነዚህ ልጆቻቸው ከነሱ የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩና፣ ኢትዮጵያንም በትምህርት ገበታ ባገኙት ዘመናዊ ዕውቀታቸው ገንብተዋት፣ በሥልጣኔ ከገፉት አገሮች ጋር አስተካክለዋት፣ከተቻለም አስቀድሟት፣ከኋላቀርነትና ከድኅነት ማቅ አላቅቀዋት፣ ለቀጣዩ ትውልድ እንዲያስረክቧት በማሰብ ነበር። ግን ያ ሁሉ ሕልም ሁኖ ቀረ። ይባስ ብሎ ደግሞ፣ **ልጆቹ እንደጀግኖች አባቶቻቸው መሆኑ ሲያቅታቸው፣ እንደማድነቅ ጠሏቸው። ብዙዎቹ ታሪካቸውን አኰሰሱ፤ ከነሱ በመወለዳቸው ተጸጸቱ፤ ጀብዷቸውን ናቁ። አንዳንዶቹ በግልጥ ባይሉትም፣ ለነጭ ባለመገዛታቸው ተቈጩ። በዚህ መልክ አገርና ወገን በማንቋሸሽና በመበታተን ተግባር በግንባር ቀደምትነት የመሩት የኤርትራ ነፃ አውጭ ድርጅቶችን ያቋቋሙት ናቸው።"**

ፕሮፌሰር ሃይሌ ላሬቦ ራሳቸውም የዚያ ዘመን ተማሪ ነበሩ ብዬ አምናለሁ፡፡ ከድሁፋቸው የምረዳው እሳቸው ያስተማራቸውን ዘውድ አለመካዳቸውን ነው። ግን ፕሮፌሰሩ አልታይ አላቸው እንጅ ሚሊዮኑን ጭቁን የኢትዮጵያን ህዝብ ከባላባታዊው አስከፊ ስርአት ነጻ ያወጡት የሚኮንኑት ያ የተማረው ትውልድ ነው፡፡ ፕሮፌሰር የታሪክ አዋቂ ናቸው፡፡ እኔም ሆንኩ ፕሮፌሰሩ ሶስት መንግስቶችን አይተናል፡፡ ሶስቱም መንግስታት የቅርብ ጊዜ ት ዝታ በመሆናቸው የሆነውን ሁሉ ስለኖርኩበት እውቀቱ እንዲኖረኝ የታሪክ ፕሮፌሰር መሆን አያስፈልገኝም፡፡ የገረመኝ ጉዳይ ቢኖር ታሪከኛ የሆኑት ፕሮፌሰር ብዙዎቻችን አስረግጠን የምናውቀውን ይህን የቅርብ ጊዜ ሃቅ ለምን ማወላገድ እንደፈቀዱ ነው፡፡ ለምን መዋሸትን መረጡ? ውሸታቸው ደግሞ ብዙ ነው፡፡ እስቲ አንድ በአንድ በኢህአፓ ላይ ያዘነቡትን ውሸት እንመልከት፡፡

ሃይሌ ላሬቦ ስለ ኢህአፓ ያላቸው ጥላቻ ጣሪያ የነካ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ወያኔን አክ ብሎ እንደተፋውም ያውቃሉ፡፡ የላሬቦ ቅኝት ያነጣጠረው ኢህአፓን ወያኔ እስመስዬ ከቀረድኩት ህዝቡ እንዲጠላው እደርጋለሁ ከሚል የሞኝ ህልመኝነት ይመነጫል፡፡

## ውሸት ሁለት፡-

ፕሮፈሰር ሃይሌ ወያኔና ኢህአፓ ተመሳሳይና ልዩ ናቸው ሲሉ የተምታታ የውሸት ታርካቸውን ሊያስተምሩን ሲደክሙ አይቼ አዘንኩላቸው፡፡ እንዴት ተደን ይሆን ኢህኢፓና ወያኔ አንድ ይሆናሉ የሚሉን ደፋሩ ፕሮፌሰር፡፡ ወያኔና ኢህኢፓን አንድ ስለመሆናቸው ሊያሳምኑን ሲነሱ በራሳቸው አባባል ገና ከጅምሩ ልዩነታቸውን ያወሩልናል፡፡

**"ኢህአፓና ህወሃት መጀመሪያው በህብረብሄርነት ሁለተኛው በጎሳነት ላይ የተመሰረቱ የማይጣጣሙ ድርጅቶች መስለው ቢታዩም በአላማቸውና በረዮታቸው ግን እንድ መሆናቸው መረሳት የለበትም፡፡"**

ለማለት የፈለጉት ኢህአፓ ከመሰረቱ በኢትዮጵያዊነት ላይ የተንተራሰ አላማ ሲኖረው ወያኔ ደግም ካፈጣጠሩ የብሄርተኛ አላማ ነበረው ነው፡፡ ጥርት ባለ አባባል ኢህአፓ በኢትዮጵያ ያለው ችግር የመደብ ስለመሆኑ ሲያስተምር ወያኔዎቹ በዘር ላይ

ያተኮረ ትግል ነው የሚያስፈልገው ብለዋል፡፡ ፕሮፌሰሩ ሁለቱ ድርጅቶች የማይጣጣሙ መስለው ይታያሉ ግ ን ተመሳሳይ ናቸው በማለት ከራሳቸው አባባል ጋር ቸኩለው ይላተማሉ፡፡ ሀቁ የወያኔ አላማ ሌላ የኢህአፓ ደግሞ ሌላ ነበር አሁንም የማይገናኙ አላማ ነው ያላቸው፡፡ የወያኔና የኢህአፓ ልዩነት የአፕልና ብርቱኳን ልዩነት አይነት ነው፡፡ ልዩነት አላቸው ባለው ምላሳቸው አንድም ናቸው ብለዋል ፕሮፌሰሩ፡፡ አንድ ናቸው የሚሉን ወያኔም ሆነ ኢህአፓ አንድ የሚያደርጋቸው ስልጣን ለመያዝ መፈለጋቸው ነው ይላሉ፡፡ ኢህአፓ ከጥንት ከመሰረቱ የስልጣኑ ባለቤት እንዲሆን የፈለገው ላባደሩን፤ ገበሬውን ባጠቃላይ ጭቁኑ የኢትዮጵያ ህዝብን ነው፡፡ ይህ ምንድነው ችግሩ ፕሮፌሰር? ወያኔ ደግሞ ስልጣኑ የኔ ብቻ ነው ብሎ ይሄው ላለፉት ሃያ ሰባት አመታት ተግባራዊ እያደረገው ነው፡፡ እንዳሉት ወያኔ በለስ ቀንቶታል፡፡ ስልጣን ያላገኘው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ለስልጣን ለመብቃት በለስ ፍለጋ አይደክምም፡፡ ያላገኘውን ድል በጉልበቱ ከወያኔ እጅ መንጭቆ ማውጣቱ አይቀሬ ነው፡፡

**ውሸት ሶስት፡-**

እንዲህ ይላል፤

> ***“ ሁለቱም ኢትዮጵያንና ኢትይዮጵያዊነትን የሚያንቋሽሹ የአባቶቻቸውንና  ታሪክን የሚያዋርዱ በአጉል ትምክህትና ተቢታቸው ያበጡ*** *“ ገለመሌ ገለመሌ ይላሉ፡፡*

ፕሮፌሰር ኢህአፓን ለምን በዚህ ክስ ውስጥ አከሉት? እስቲ ኢህአፓ በኢትዮጵያ ጠላትነት ላይ የተናገረውን ወይም ያሰፈውን እንደማስረጃ ያቅርቡ፡፡ የሚኖሩበት አገር እንኳን ኢህአፓ ብርቱ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ድጋፍ ሰጥቶትም አያውቅም፡፡ ወያኔ እንኳ ኢህአፓን **“አባይ ኢትዮጵያ”** እንደሚያደርገው አልሰሙም? አላነበቡም? ኢህእፓ ለኢትዮጵያና ለዘዝቧ መስዋእትነትን የከፈለውና እየከፈለ ያለው ለአገሩና ለህዝቡ ካለው ጠንካራ ፍቅር መሆኑን ህሊና ካለዎ ይቀበሉት፡፡ ኢህአፓ ኢትዮጵያዊነቱን ለመግለጥ ታሪክ ማጥናት አይጠበቅበትም፡፡ ትግሉን ለዘመናት ሸሽተው ወፈር ያለ ዶላር ለማግኘት እርሶ ከኮሌጅ ወደ ኮሌጅ ሲንሸራሸሩ ኢህአፓ ግን የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ለማስከበር በሺህ የሚቆጠሩ አባላቱንና ደጋፊዎቹን ሰውቷል፡፡ የኢህአፓን ኢትዮጵያዊነት ለመረዳት ከፈለጉ ፕ**ሮግራሙን** ያንብቡ፤ **የፍኖተ ራዲዮ** ስርጭትን ያዳምጡ፤ የድርጅቱን ልሳን የሆነውን **ዲሞክራሲያ** የዘመናት እትሞቹን አገላብጠው ያንብቡ፡፡ የታሪክ አዋቂ ያለመረጃ መናገርና መጣፍ የለበትም፡፡ ያስንቃልም፡፡ ኢህአፓ በፕሮግራሙ አንቀድ እንድ እንዲህ ይላል፤፡

> **“መሰረታዊ አላማ፟ የኢትዮጵያ ህዝብ ሉ አላዊንትና የስልጣን ምንጭነት በህግ የሚረጋገጥበት፤ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ <u>የህዝብና የአገር አንድነት የሚጠበቅበት፤</u> የእምነትና የሃሳብ ነጻነት የሚከበርበት በህዝብ ነጻና ርቷዊ ምርጫ የሚቋቋም ፌዴራዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ መመስረት፡፡”**

ይህ የኢህአፓ አልፋ ኦሜጋ መመሪያው ነው፡፡ ዛሬ ያለው ሳይሆን ከምስረታው ጀምሮ የወጠነው መመሪያው ነው፡፡ ፕሮፌሰሩ ኢህአፓን ያለመውደድ መብት አለዎት፡፡ በድርጅቱ ላይ ግን መዋሸት አላስፈላጊ ነው፡፡ አላስፈላጊ ከመሆንም ባሻገር ያቀላል፡፡ ያዋርዳል፡፡

**ውሸት አራት፡-**

ደግሞ ቀይና ነጭ ሽብርን አስመልክቶ ፕሮፌሰሩ እሳዛኝና አስከፊ ውሸት ነዝተዋል፡፡ እንዲህ ይላሉ በድፍረት ሃቅን ረግጠው፡

> “ ሆኖም እብዛኛዎች ድርጅቱ ለስውር አላማው ሲል የፈጠረው ነጭ ሽብር የተባለ የግድያ መፈክሩ ሰለባ በመሆን ለንግልትና ለእልቂት ሲዳረጉ ከመሪዎቻቸው ራሳቸው በከፈቱት ጦርነት ጥቂቶቹ ሲሞቱም ብዙዎቹ ግ ን እቅዳቸው ሲባክን እንደምንደኛ እረኛ ተከታዮቻቸውን ቀይ ሽብር በተባል ጠላታቸው እጅ ጥለው ጓዛቸውን ጠቅልለው ወደ ውጭ እገር እንደፈረጠጡ “

የድርጅቱ ስውር አላማ የሚሉት ምንድነው? ለርሶም ሚስጢር ነበርን? ወይስ ስውር አላማ ማለቱ እንባቢዎችን ለማሳመን ዘዴ ፈልገው ነው፡፡ ኢህአፓ ከድርግ ጋር ሲፋለም ስውር አላማ የሚባል ነገር አልነበረውም፡፡ አላማው ደርግን ከህዝብ ጫንቃ ላይ ለማውረድ ነበር ኢህአፓ የታገለው፡፡ ይህ ስውር ሴራ ከሆነ እሰየው፡፡ ኢህአፓ ሽብርን አልጀመረም፡፡ ትክክለኛ ታሪኩን ለማንበብ ያልታደሉ የታሪክ ምሁር በመሆኖ እየተገረምኩ ቢሆንም ግን እንዲህ ሆነ ብሎ አፍን ከመክፈት በፊት

ተገቢውን ሃቅ ማንበቡ ተገቢና ትክክልም ነው የሚል ምክር መወርወር እፈልጋለሁ፡፡ ለፕሮፌሰር ላሬቦ ይህ የሚሰወርባቸው ባይሆንም " **እውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት እይነቃም"** ካልሆነባቸው በስተቀር፡፡ ስለ ነጭና ቀይ ሽብር ከመተንፈስ በፊት የመጀመሪያ ጥይት የተኮሰው ማን እንደሆን በሚገባ መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ኢህአፓ አንድ ጥይት ስለተቶከሰበት ተጣድፎ እርምጃ አልወሰደም፡፡ የደርግ ና የመኢሶን ጭፍጨፋ ሲያይልበት ራሱን ለመከላከል ርምጃ ለመውሰድ ተገዷል፡፡ ኢህአፓ ምን ማድረግ ነበረበት? እጁን አጣጥፎና አንገቱን ደፍቶ የደርን ና የመኢሶንን ግድያ አሜን ብሎ መቀበል ነበረበት? ጥያቄው ለርሶ ነው ፕሮፌሰር፡፡

**ውሸት አምስት፡-**

ፕሮፌሰሩ ኢህአፓን ጭራቅ ለማድረግ እንዲህ ሲሉ ሴራ ይወረውራሉ፡፡

> " እቶ ክፍሉና አቶ ተስፋዬ ደበሳይ ሰውየውን ከገደሏቸው በሃላ ራሳቸውን እጃቸውን እግራቸውንና ሌላውን እካላቸውን ለየብቻው ቆራርጠው በጆኛ ከትተው በመንገድ ይዘውት ሲሄዱ ተይዘው ሁለቱም ሸሽተው እንዳመለጡ **ይነገራል**፡፡"

ፕሮፌሰር ላሬቦ ለመሆኑ ይህ ድርጊት የተካሄደው **የት** ነው? **መቼ** ነው? ተይዘው አመለጡ ማለት ምን ማለት ነው? ሬሳው ያለበትን ጆንያ ይዘው አመለጡ ወይስ ትተውት? ሬሳውን የያዘውን ጆንያ ትተው ከሆነ የደርግ መንግስት ይህን ወሬ ለምን ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታው ሳይጠቀምበት ቀረ? ለነገሩ ፕሮፌሰሩ ሲደመድሙ **ይነገራል** የሚለው ቃላቸው አባባላቸው ተረት ስለመሆኑ ማረጋገጫ ይሆናልና ውሸታቸውን ንቆ መተው ይመረጣል፡፡

**ውሸት ስድስት፡-**

> " ኢህአፓ የኢትዮጵያን ፍዳሜ በሚከተለው ምድረገነት ስብከቱ በአገር ስሜት የነደደውን ዘመናዊ ትምህርቱን ከነባሩ ስርአትና ወግ ማጣጣም ያቃተውን የቦዘኔንና የህልመኛውን እንዲሁም የግልቱንና የገልቱን ወጣት ቀልብ በሰፊው ሊስብ እንደበቃ የማይካድ ሃቅ **ይመስለኛል**፡፡"

ፕሮፌሰር ሃቅ ይመስለኛልና ሃቅ ነው ለየቅል ናቸው፡፡ ኢህአፓ የመላውን ኢትዮጵያውያንን ፍቅር ያተረፈ የማይካድ ሃቅ ይመስለኛል ሳይሆን የማይካድ ሃቅ ነው ብለው ያርሙት፡፡ ኢህአፓ የኢትዮጵያን ህዝብ ከዳር እስከ ዳር ለለውጥ ያንቀሳቀስ ድርጅት ነው፡፡ አባላቱ ከሁሉም ህብረተሰብ የተውጣጡ ናቸው፡፡ ከንባታው ጉራጌው አደሬው ወላሞው ዶርዜው ኩናማው ኦሮሞው እማራው ትግሬው ኤርትራዊው ወዘተ ወዘተ፡፡ ከተራ አባላቱ እስከ መሪዎቹ ለናት አገራቸውና ለህዝቧ ሉኣላዊነት ሲሉ የህይወት መስዋእትነት ከፍለዋል፡፡ ስፍር ቁጥር የሌልው ኢትዮጵያውያን የድርጅቱ እባል ሲሆኑ እርሶ እንዴት ሊዘለሉ እንደቻሉ ባይገባኝም ምናልባት ከቦዘኔው ከገልቱው ከእንግልቱ ውስጥ ስላላነበሩ ይመስለኛል፡፡ ኢህአፓ ያቀፈው ቦዘኔ ገልቱ ግልቱ ነው ለማለት ቢፈልጉም ወታደሩ ገበሬው ላብ አደሩ መምህሩ ተማሪው ምሁሩ ወጣቱ ሴቱ ያቀፈውና ያፈቀረው ድርጅት ስለመሆኑ ቋቅ ቢሎትም ሃቅ ነውና መቀበል አለቦት፡፡

ለመሆኑ ዛሬ ኢህአፓን ለመኮነን ለማጥላላትና ስንት መስዋእትነት የከፈለበትን ታሪኩን ጥላሸት ለመቀባት ለምን ተነሱ? እንዲያው **አድርባይ ምሁር ሲያረጅ ጃርት ይሆናል** ማለቱ ማጋነን አይደለም፡፡ የኢህአፓን ህዝባዊነት ለማሳነስ ኢህአፓ እንዲህ ነበር አልነበር በማለት ያቀረቡት ውሸት የሚያስታውሰኝ " **ድንጋይ ላይ ከወደቅህ ትጎዳለህ፤ ድንጋዩም ቢወደቅብህ ትጎዳለህ**" የሚለውን አባባል ሆኖብኛል፡፡